*__የታረዱት ነፍሳት ጩኸት__*

# __በሊቢያ ለተሰውት ኢትዮጵያውያን በዋሽንግተን ሞኑመንት ላይ May 10, 2015 የተደረገውን መታሰቢያ ከአዘጋጁት ማህበራት ህብረት የወጣ መግለጫ__

ይህ መግለጫ በሊቢያ እና በደቡብ አፍሪካ ስለተገደሉት ወገኖቻችን፤ በዋሽንግተን ሞኑመንት ላይ May 10, 2015 የተደረገውን መታሰቢያ ከአዘጋጁት ማህበራት ህብረት የወጣ መግለጫ ነው።

1ኛ:- በሊቢያ እና በደቡብ አፍሪካ በግፍ ለተገደሉት ወገኖቻችን May 10, 2015, ዋሽንግተን ዲሲ ብሔራዊ አደባባይ [monument] ላይ "የታረዱት ነፍሳት ጩኸት" በሚል ርእስ የኮሚቴው ህብረት አዘጋጅቶ ባቀረበው

2ኛ:- ቆይቶ በሌላ ጎራ "ዲያብሎስን እንቢ በሉ ከናንተ ይሸሻል። እግዚአብሔርን እሺ በሉ ወደ እናንተ ይቀርባል" በሚል ርእስ June 14, 2015 በኬና ቴምፕል በመምህር ዘበነ እንደገና ተዘጋጅቶ በቀረበው

በአካል ተገኝቶና በሩቅ ሆኖ ሁለቱንም ዝግጅቶች በተለያዩ መንገዶች ለተመለከተው ህዝብ የተደበላለቁ መልእክቶችን አንጸባርቋል። __በሞንመንቱ የተካሄደውን ዝግጅት ለህዝብ ያቀረበው ኮሚቴ ይህን የተደበላለቀ መንፈስ ሳያጠራ በዝምታ ማለፍ ከመንፈሳዊነትና ከሞራል ውጭ ሆኖ ስለተሰማው ይህን መግለጫ ለማውጣት ግዴታ ሆነበት።__

የሚታረዱ ከብቶች ለመታረድ ወደ ሚሄዱበት ቄራ እንደሚነዱ እንስሳት ሆነው ወገኖቻችን ባረመኔወች ሲነዱ የህብረቱ ኮሚቴ ባያቸው ቅጽበት፤ መስቀሉን ተሸክሞ ወደሚሰቀልበት ጎልጎታ የሄደውን የክርስቶስን ነጸብራቅ ተመለከተ። ከሚታረዱበት ቦታ ደርሰው በአረመኔዎች ሲታረዱ የደረሰባቸው ስቃይ፤ መለኮት በተወሀደው በክርስቶስ ሰውነት ላይ ከደረሰው በሰባዊ ቋንቋ ሊገለጽ የማይቻል ስቃይ እንደሆነም ተረዳ።

በወገኖቻችን ላይ የደረሰውን አሰቃቂ ግድያ በጌታችን ላይና በናቱ በቅድስት ድንግል ማርያም ከደረሰው በላይ አድርጎ የህብረቱ ኮሚቴ የተመለከተው፤ በጌታችን ላይ የደረሰበትን ዘግናኝ ሁኔታና በእናቱ ቅድስት ድንግል የደረሰባትን መከራና ስቃይ ዝቅ አድርጎ በመመልከት አይደለም። __ክርስቶስ ለሰው ልጅ ክብር ተገርፎና ተሰቅሎ እንደሚሞት አስቀድሞ በነብያት ገልጾ፤ ራሱ ፈቅዶና አቅዶ ያደረገው በመሆኑ ነው። መከራውን የተሸከመበት ሰውነትም መለኮት የተወሀደው በመሆኑ መከራውንና ስቃዩን ለመሸከም አስችሎታል ለማለት ነው።__

እመቤታችን ቅድስት ድንግልም በአንዱ ልጇ ላይ የደረሰውን ስቃይ ባየችው ጊዜ የተሰማትን መከራ ማቃለልም አይደለም። __ገና በእቅፏ ሳለ "የሚደርስበትን ሁሉ መከራና ስቃይ በልቧ ትጠብቀው ነበር" (ሉቃስ 2:51) መከራውም ሰይፍ ሆኖ "ልብሽን ይሰነጥቀዋል" (ሉቃስ 2: 35) እየተባለ አስቀድሞ ተነግሯት ስለነበርና የቅድስናዋ ረድኤትም እንደሚደግፋት በማመን ነው።__

ዛሬ የምናስባቸውን ሰማእታት የወለዱ ኢትዮጵያውያን እናቶች ግን፤ ልጆቻቸው ተወልደው ባደጉበት፤ እትብታቸው በተቀበረበት መንደራቸው ላይ ከሚደርስባቸው መከራና ስቃይ አመለጡሉን ብለው ደስ ብሏቸው በህሊና እረፍት ላይ ሳሉ፤በተሰደዱበት አገር እየታረዱና እየተቃጠሉ ሲሞቱ ባይናቸው ሲያዩ፤ የሚሰማቸው መከራና ሥቃይ፤ የልጇ ስቃይ ተነግሯት በልቧ ስትጠብቀው በነበረችው በእመቤታችን ላይ ከደረሰው መከራ ጋራ ሲነጻጸር፤ ያልጠበቁትና ያላሰቡት ከመሆኑ በላይ፤ እንደ እመቤታችን የልዑል ኃይል ግርጃ ስለሌላቸው ነው።

ይህን ዘግናኝ ተደራራቢ መከራ የሰማና ያየ ዓለም ሁሉ በግሉም ሆነ በቡድን፣ የተሰማውን ጥልቅ ሀዘን በተገናኘበት ቦታ ሁሉ በየቋንቋው ተነጋግሮታል፤ በየስሜቱም ገልጾታል። ሰማዕታቱ ከኛ ጋራ ያላቸው ግኙነት በቤተ ሰብ ዝምድና የተሳሰርን ስለሆነ፤ በሰባዊነት ተሰምቶት ካዘነው ከሌላው ዜጋ ይልቅ ሀዘኑ በኛ ላይ እጅግ ይከብዳል። ከነሱ ጋራ የተሳሰረው ሰውነታችን እንደ ሰም ቀልጧል፤ ሰማይ ተደፍቶብናል፤ ፀሐይ ጨልማብናለች፤ መሬት ተንዳብናለች። ይህንን ለመግለጽ፤ ከእናት ኢትዮጵያ አገራችን ማህጸን የፈለቅን ሁሉ በጎሳ፤ በቋንቋና በእምነት ያለንን ልዩነት ሰብረን፤ በአንድነት ተሰብስበን እርማችንን እናውጣ በሚል ወገናዊ መንፈስ ለፖሮቴስታንት ክርስቲያኖች እና ለሙስሊም እምነት ተከታዮች ወገኖቻችን ጥሪ አደረግን።

ጥሪያችን የደረሳቸው ወገኖች ሁሉ "ከተገደሉት ወገኖቻችን ጋራ ያለን የሥጋና ደም ዝምድና ከናንተ የተለየ አይደለም፤ ሀሳቡ ቀደም ብሎ መጥቶላችሁ ስለጠራችሁን እናመሰግናል። በዜግነታችን እንደናንተ ጠሪዎች ሆነን ሌላውን እንጠራለን። ተጠሪም ሆነን በቦታው በመገኘት የጋራ እርማችንን እንወጣለን። ለዝግጅቱ የሚያስፈልግ ነገር ካለም እንረዳለን" በሚል ወገናዊ ስሜት ፈቃዳቸውን ገለጹልን።

የሁሉንም ወገን ስምምነትና ፈቃድ ካገኘን በኋላ፤ የቤተ ክርስቲያናችንን መርሆ ሳይለቅ "አምላኬን ለምን እረሳሀኝ እለዋለሁ" ( 41፡ 9) እያለ ዳዊት በመከራው ያንጎራጎረውን መሠረት በማድረግ፤ የኢትዮጵያን የሁሉ እናትነትና፤ የታረዱት ኢትዮጵያውያንም የሁሉም ወንድምነታቸውን በሚገልጽ እና ሁሉንም በሚያሳትፍ መንገድ፤ የነፍሳቸውን ጩኸት እያንጸባረቀ፤ በታረዱበት ዘመንም፤ እናታቸው ኢትዮጵያ በምን ሁኔታ እንዳለች ከሞላ ጎደል በሚገልጽ፤ ታሪክም ሆኖ አስተማሪነቱ ለቀጣዩ ትውልድ እንዲያገለግል በሚያስችል መንገድ ዝግጅቱ ተጀምሮ እንዲፈጸም ኮሚቴው ወሰነ።

በሰብሰባው የነበሩት እነ መምህር ተስፋዬ መቆያ "ይህ አዝማሚያ ከኢህአዴግ መንግሥት ጋራ ያጋጨናል" የሚል ሀሳብ አቀረቡ። "የፈጣሪ ትልቁ ጉዳይ በአምሳሉ የፈጠረው ሰው ነው። ሲወድቅም፤ አምላክ የሰውነትን ባህርይ በመዋሀድ እንደሰው በመውደቅ ከወደቀበት ያነሳው ክቡር ነው። ታዲያ በፈጣሪ እጅግ የተከበረ ሰው በኢህድግ አልተዋረደም? ነው የምትሉት?" የሚል ጥያቄ ከኮሚቴው ቀረበላቸው። እነ መምህር ተስፋዬ "አዎ ኢትዮጵያውያን የተዋረዱበት ዘመን ነው" ብለው መለሱ። "ታዲያ አይነገር አይገለጽ እንዴት ትላላችሁ?" የሚል ጥያቄ ኮሚቴው አቀረበላቸው። "በኢትዮጵያ የጀመርነው እቅድ ስላለን በዚህ መንግሥት ሰው ተዋረደ ብለን ብንናገር ከመንግሥት ጋራ እንጋጫለን" የሚል ሀሳብ እነ መምህር ተስፋዬ አቀረቡ። "ሳትደብቁ እውነቱን በመናገራችሁ እናመስጋናችኋል። ነገር ግን ለናንተ ወቅታዊ እቅድ ስትሉ፤ የጠቅላላውን ህዝብ ጉዳት አታፍኑ። የተደራረበ ኋላፊነት ያለባትን የቤተ ክርስቲያናችንን ልሳን ለመዘጋትም አትሞክሩ። በኢትዮጵያ የዘረጋችሁትን እቅድ ከገለጻችሁልንና ተገቢነቱንም ከተረዳን ልንረዳችሁም ፈቃደኞች ነን። ነገር ግን መንግሥት ሰው ገድሎ አትግደል ስንል ፖለቲካ ገባችሁ አትበሉን፤ ሰው በግፍ ሲበደል፤ ሲታሰር፤ ሲገደልና፤ ሲሰደድ፤ አትበድሉ፤ አትሰሩ፤ አትግደሉ፤ አታሳዱ ብሎ መናገር፤ ነገረ_መለኮት ነው። ከዚህ ሌላ የካህናት ተልእኮ የለም። አለመናገር ዝም ብሎ ማለፍ ግን ነገረ_ሰይጣን፤ የሰይጣን ሠራዊት ተልእኮ ነው። የሀሰት መምህራን በዝተው፤ ውሸት በህዝብ ላይ ሲሰፍን፤ ሰው በግፍ ሲደበደብ፤ ሲታሰር፤ ሲገደልና ሲሰደድ ዝም ካላላችሁ ፖለቲከኞች ሆናችሁ" እያለ ያስተማራችሁ ካለ፤ የሰው ጠላት የሆነውን የሰይጣንን ፖለቲካ የሚያራምድ ሰው ነው። መለኮት በሰማያዊ መንግሥቱ ለሰው ልዩ ክብርና ልዕልና የሰጠበትን ፍቅር (ነገረ መለኮት)፤ ሰውን ከሚያሳድድ፤ ከሚያዋርድና ከሚገድል ነገረ_ሰይጣን ለይታችሁ እወቁ" ሲል ኮሚቴው እነ ተስፋይ መቆያን መከራቸው።

እነ መምህር ተስፋዬ መቆያ ከላይ የተገለጸላቸውን ከሰሙ በኋላ "ከኢህድግ መንግሥት ጋራ በማያገጨን መንገድ ስለ ሰማእታቱ የሚዘጋጀውን በ ISIS ተገደሉ ብለን እንለፈው። ህዝቡ መንግሥትን በሚቃወምበት በሌላ ወቅት ግን፤ ከህዝቡ ጀርባ ሆነን ህዝቡን በመደገፍ እንገፋለን" የሚል አማራጭ አቀረቡ። ኮሚቴውም "ቤተ ክርስቲያናችን ያስተማርችን የምናምንበትን ከላይ የተገለጸውን ነገረ መለኮት በግልጽ መናገርና ማድረግ ነው። በግልጽ የማናደርገውን ነገር ለምንድነው ህዝቡ እንዲያደርገው በጀርባ ሆነነ የምንገፋው? እኛ ለመጨበጥ የፈራነውን የጋለ ብረት ለምንድነው በምእመናኑ እጅ ለመጨበጥ የምንሞክረው? ይህማ "የማይገለጥ የተከደነ፡ የማይታወቅ የተሰወረ ምንም የለም" ብሎ ክርስቶስ የተናገረውን

አለማወቅ ከካህናት ባህርይ መራቅ ነው" የሚል መልስ ተሰጣቸው። እነ መምህር ተስፋዬም "ይህ አቀራረብ ከመንግሥት ጋራ ስለሚያጋጨን በመንመንቱ ላይ የሚካሄደውን አንሳተፍም" ብለው ውሳኔያቸውን ገለጹ። ከዚያ በኋላ "መምህር ዘበነ ተዝካር እናውጣ የሚል ሀሳብ አቅርቦልናል። ይህንን ሀሳብ ከነ አቡነ ፋኑኤል ጋራ ለመነጋገር ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን እንድንሰበሰብ ስለ ስለጠራን ወደ ስብሰባው እንሄደለን" ብለው በሞንመንቱ ላይ የተካሄደውን አልተሳተፉም። በውጭ ሆነው የ40 መታሰቢያ ተዝካር እናደርጋለን እያሉ ማስወራታቸውን ቀጠሉ። ዝግጅቱ ከተከናወነበት ቀን በኌላ በማግስቱ በሞንመንቱ ላይ የተካሄደውን ለመቃኘት በተደረገው አጭር ስብሰባ ላይ፤ የእነ መምህር ተስፋዬን በዝግጅቱ ላይ አለመታየት ከኮሚቴ መካከል ቅሬታ ቀረበ። አንድ በስብሰባው የተገኘ የነ መምህር ተስፋዬ ቡድን አባል፤ "መምህር ተስፋዬ በሞንመንቱ በተከናወነው ላይ ያልተገኘው፡ የተጣሉ ባልና ሚስት ሲያስታርቅ ነው" ብሎ ተናገረ።

ከዚህ በላይ የተገለጸው፤ ዝግጅቱ ከተጀመረበት ጀምሮ እስኪፈጸም ድረስ እንዳይከናወን የነበረውን ውዝግብ ለማሳየት ሲሆን፤ መምህር ዘበነ በዚህ ሁሉ ሂደት የተከናወነውን አልሰማሁም ያለውን ቃል ውሸት እንደሚያደርገው የሚጠራጠር ይኖራል ተብሎ አይገመትም። እነ መምህር ተስፋየ በቀጥታ፤መምህር ዘበነ ደግሞ በተዘዋዋሪ መንገድ የተካሄደውን ስብሰባ ሲካፈሉ ለነበሩ ሰዎች ይቅርና በዋሽንግተን በቨርጅንያና በሚሪላንድ ዙሪያ የሚኖር ወገን ስለ ዝግጅቱ እንዲሰማ የጥሪው ድምጽ የተሰራጨበትን እለታትና በተደጋጋሚ መገለጹን ከዚህ በታች እናቀርባለን።

1ኛ:- ሰማዕታቱ በተገደሉበት ዕለት የዳግም ትንሳኤ ጠዋት (April 19, 2015) በርዕሰ አድባራት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ስለ ሰማዕታቱ አሰቃቂ ግድያ ለህዝብ ተገለፀ።

2ኛ:- ዓርብ April 24, 2015 በቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሰፊ የሀዘንና የመታሰቢያ ጸሎት ተደረገ በኋይት ሀውስ ወይም በሞንመንቱ ለዓለምም ለማሰማት የሚያስችል መርሀ ግብር እንደሚዘጋጅ ተነገረ። ዓርብ መምህር ዘበነም በቦታው ስለነበረ፤ (ቅዳሜ April 25, 2015) በመድህኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ጸሎት እናደርጋለን የሚለውን ብቻ ተናገረ እንጅ፤ ቦታ ተከራይቶ ሁሉንም በሰፋት የሚያሳትፍ እቅድ እንደነበረው አልተናገረም።

3ኛ:- መምህር ዘበነ በመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ባደረገው የጸሎት መርሀ ግብር ላይ የተገኙ ካህናት በሞንመንቱ ላይ እንዲካሄ ስለታቀደው ዝግጅት ነግረውታል። Flyer ም በእጁ ተቀብሏል።

4ኛ:- እነ መምህር ተስፋዬ መቆያ ካስተዳደር በደል ሲሸሹ ተገደሉ ማለት ኢህድግን የሚያስቆጣ ነገር ነውና አንተባበርም፤ ያሉትና፤ የመምህር ዘበነን እቅድ ብቅ ያደረጉት ፤ April 28, 2015 ማክሰኞ በተደረገው ስብሰባ ላይ ነበር።

5ኛ:- በሞኑመንቱ ላይ ስለሚደረገው ዝግጅት በየተቦታው ማስታወቂያ(Flyer) ተበተነ።

6ኛ:- ለየአብያተ ክርስቲያናትም ደብዳቤ/E-mail ተላከ።

7ኛ:- በየድረ ገጾችም ጥሪው ተላለፈ።

ከዚህ በላይ የገለጽናቸው በመምህር ዘበነ የተከሰቱት ስህተቶች በህዝብ ላይ የማያስፈልግ ውዝግብ ፈጥረዋል። ለምሳሌ:- በ Demtse Tewahedo ሬዲዮ ራሱ መምህር ዘበነ በየሳምንቱ በሚያቀርበው ዝግጅት ላይ ከአንድ አድማጭ ለራሱ ለመምህር ዘበነ የቀረበው ጥያቄ፤ በራሱ በመምህር ዘበነ ላይ የከሰተው ውጥረት አልሰማሁም የምትለውን የሀሰት ቃል ካንደበቱ ማውጣቱ ጉሉህ ማስረጃ ነው።

ጠያቂውን ያቀረቡት ወገን "እኔ ቆራቢ ነኝ በሞንመንቱ በተደረገው ዝግጅት ላይ ያልተገኛችሁበት የሰማሁት ምክንያት አለ። ጥያቄውን ሸፋፍኖ ለማለፍ ከመሞከር ይልቅ መመለሱ ይጠቅማል" የሚል አስገዳጅ ጥያቄ ሲያቀርቡለት "አልሰማሁም" ብሎ መምህር ዘበነ የሰጠው የተዛባ መልስ፤ "እምነታችንን ከምንለው፡ጥ ህይወታችን ትለፍ" ብለው ከተሰውለት ሰማዕታትነት ጋር ዝግጅቱን ምንም ግንኙነት የሌለው አድርጎታል። ለወገን ለዜጋ እየተጋረደች ከፉ ዘመን ባሳለፈችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሰማእታቱ አሰቃቂ ግድያ ላይ ይህ ውዝግብ መከሰቱ በሰሚው ላይ ተጨማሪ ሀዘን ሆኖበት ሰንብቷል። እንዲሳተፍ በግሉ የደረሰውንና ለቤተ ክርስቲያኑም የተላከውን ጥሪ ከመካድ ይልቅ መሳተፍ አልፈለኩም ማለት በቀለለ ነበር። በዚህ ሁሉ መንገድ በከተማው ሲሰራጭ የነበረውን አልሰማሁም ማለቱ ብቻ ዋሾ ያደርገዋል። ህዝበ ክርስቲያኑ ይህን ሁሉ መለስ ብሎ ሲያስበው በጥያቄ ብቻ የሚያልፈው እንደማይሆን መገመት ሞኝነት ይመስላል።

እግዚአብሔር የሰላምና የመረጋጋት ዘመን ሰጥቶን እውነተኞች የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት ነጻነት አግኝተው በመሰብሰብ የጠመመውን አቃንተው፤ የተበታተነችው ቤተ ክርስቲያናችን ወደ አንድነት እስክትመጣ ድረስ፤ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም "ያባትህ ቤት ሲበዘበዝ አብረህ በዝብዝ" በሚለው ነገረ_ሰይጣን የሚመሩትን እየታዘበ፤ አትግደል በሚለው ነገረ መለኮት ራሳቸውን ጠብቀው በማገልገል ላይ ላሉት ቀሳውስት ለቤተ ክርስቲያናችን ቅድስና የሚያስቡ ዜጎች ሁሉ፤ ተገቢ ክብራቸውን ይሰጣሉ ብሎ የተባበረው ኮሚቲ ያምናል።

የህብረቱ ኮሚቲ በሞንመንቱ ላይ ያደረገው፤ በወገናዊነት ንጹህ ስሜትና ህሊና ተነሳስቶ እንጂ፤ ጥሪውን በተሰበረ ልብ ተቀብሎ ከዝግጅቱ ላይ ከተገኘው ሁሉ ወገን ለሞቱት ወገኖቻችን የበለጠ ቅርበት አለን ብለን አልነበረም። በእምነታቸው የተሰየፉትን ጸሎተ ፍትሐት በማድረግ እናጸድቃለን ብለንም አይደለም። መታሰቢያቸው (ዝክራቸው) በህዝብ ህሊና የተመዘገበው ያማሚተቸው ታሪክ ስለሆነ ለመታሰቢያም ብለን አልነበረም። ከኢህአዴግ መንግሥትም ይሁን ከሌላ አካል ወቀሳና ክስ ይደርስብናል ወይም ያስመሰግነናል የሚል ሀሳብም አልነበረንም።

በዝግጅቱ ላይ የተካሄደው በቤተ ክርስቲያናችን ስርአት የሰማዕታትነታቸውን ሁለንተና አልገለጸምና በዚህ መንገድ መቅረብ ነበረበት፤ የሚል እርማት ቢቀርብልን ኖሮ የህብረቱ ኮሚቴ እርማቱን በትህትና ተቀብሎ በድጋሚ በቀረበው ዝግጅት ላይም በተባበረ ነበር። ነገር ግን በነ መምህር ዘበነ ዘግይቶ የቀረበው ዝግጅት፤ በወገናዊ መንፈስ በሞንመንቱ ለቀረበው ዝግጅት በአንጻ መንፈስ የቀረበ ስለመሰለ፤ ሁለቱ በንጽጽር መልክ ለህዝብ እየቀረቡ እስካሁን በመካሄድ ያለው ውዥንብር ተከስቷል። በሞንመንቱ ላይ በተካሄደው ዝግጅት ላይ ሰማእታቱን የማይገልጽ ስህተት ካለ ይቅርታ እየጠይቅን፤ በሌላ ጎራ ስለቀረበው ግን ከኮሚቴው ህብረት ቁጥጥር ውጭ መሆኑን ለመግለጽ ያቀረበነውን መግለጫ ከዚህ በታች ባሰፈርነው ሀሳብ እንደመድማለን።

***መደምደሚያ***

ይህን ዘግናኝ ተደራራቢ መከራ የሰማና ያየ በዓለም ያለ ሰው ሁሉ በሰባዊነት ብቻ የተሰማውን ጥልቅ ሀዘን በተገናኘበት ቦታ በግሉም ሆነ በቡድን በቃል ተነጋግሮታል በስሜትም ገልጾታል። እኛ ኢትዮጵያውያን ከሰማእታቱ ጋራ ባለን ቤተ ሰባዊ ዝምድና፤ ሰውነታችን እንደ ሰም ቀልጧል፤ ሰማይ ተደፍቶብናል፤ ፀሐይ ጨልማ ሆናብናለች፤ መሬት ተንዳብናለች።

1ኛ:- ይህን የደረሰብንን መከራ በጎሳ፤ በቋንቋና በእምነት ሳንለያይ ለመሸከም ጥንካሬውን እንዲያድለንና ዳግምም እንዳያሰየን ወደ አምላካችን ለማቅረብ።

2ኛ:- በኢትዮጵያውነታችን ብቻ የደረሰብን መከራና ሥቃይ የከበደብን መሆኑንም ለዓለም ህዝብ ለመግለጽ

3:- ሰማዕታት ወገኖቻችን ለምታልፈው ዓለም ብለው እምነታቸውን ሳይለውጡ በህይወታቸው ከመሰከሩላት ሰማእትነት እንድንማር፤ በእውነት ጸንተን በመቆምም ለእምነታችን ለወገናችን ለአገራችን እንድንመሰክር

4ኛ:- እየደረሰብን ያለው መከራ እንዳይደጋገምብን ማስቆም በሚያስችል መንፈስ በግልም በህብረትም ዜግነታችን የሚጠይቀንን ለማድረግ እንድናስብ ነበር።

መምህር ዘበነ በመንመንቱ ስለተደረገው አልሰማሁም እያለ ከመዋሸቱ ጋራ፤ ለሰማእታቱ የ40 ቀን ትዝካር ብሎ ያቀረበው ፤ የንስሀ መንፈስ በሌላቸው ይልቁንም የንስሀን መንገድ በሚዘጉ፤ ብጹዕ በሚል ቅድስና በተላበሱ በአባ ፋኑኤልና የጋብቻን ቅድስና ባረከሱ፤ በማርከሳቸውም፤ ማፈር ሲገባቸው እንደቅድስና እየቆጠሩ በሚያቆምሱ፤ አትዘሙቱ አትዋሹ ብለው የሚገስጹትን ምእመናን ባደባባይ በሚከሱ፤ ከነገረ መለኮት በራቁ ሰዎች ነው። የሰማዕታቱ የ 40 ቀን መታሰቢያ እነዚህን በመሰሉ ሰዎች ጸሎትና ቡራኬ ተጀምሮ መዘጋቱ፤ የሰማእትነታቸውን ትርጉምና ምሳሌነት ጠለሸት አልብሶታል።

ከላይ የተገለጸውን ሁሉ ተመልክቶ፤ በመታዘብና በማዘን ላይ እንዳለው ህዝብ፤ የኮሚቴው ኅብረትም እጅግ ማዘኑን እየገለጸ የነፍሳትን ጩኸት የሚሰማ አምላክ፤ እውነትን እየሳቱና ህዝብን እያሳቱ ወደ ባሰ ችግር የሚከቱትን ሰዎች ይግታልን፤ በጭፍን፤ በግል ጥቅም፤ በዝምድናና በጓደኝነት የሚከተሏቸውንም የወገኖቻችንን ዓይነ ልቡና ያብራልን በማለት ይህን መግለጫ ለሚመለከተው ሁሉ ወገን እናቀርበላን።